# የፖለቲካ ሽሙጥ ክፍል 1

## የጉድ እኮ ነው !!!

የጉድ እኮ ነው በየቡድኑ፣ በየድርጅቱ፣ በየፓርቲው፣ በየጎሣው፣ በየጎጡ፣ በየቋንቋው፣ በየረድፉ፣ በየቀልቋዩ፣ በየመልኩ፣ ሁሉም ፖለቲከኛ ሆኖ ያጓራል።

**የጉድ እኮ ነው! የጉድ እኮ ነው!** አስመሳዩ፣ ተለጣፊው፣ ግልብጡ፣ አንጃው፣ አደንዛዡ፣ ጎንጓኙ፣ ወሮበላው፣ ድንዛዡ፣ አፋዳሹ፣ የውስጥ አርበኛው፣ ለስልጣን የቋመጠው፣ አደርባዩ፣ ዘረኛው፣ ገንጣዩ፣ አስገንጣዩ፣ ጠባቡ፣ አተራማሹ፣ ባንቲስታቱ፣ አሸርጋጁ፣ ቅሌታሙ፣ ወራዳው፣ አረኾው፣ ሰርጎ ገቡ፣ ቅጥረኛው፣ አቀንቃኙ፣ ቀላዋጩ፣ ለማኙ፣ ከሀዲው፣ አጭበርባሪው፣ ውሸታሙ፣ ቀጣፊው፣ አታላዩ፣ ሥርዓት አልበኛው፣ መሸተኛው፣ ሴሰኛው፣ መለኮኑ፣ ችግር ያንቀራጠጠው፣ ዱቤ የከበደው፣ ሞርጌጅ ያስጨነቀው፣ ባንክ ዘራፊው፣ የሙስና ቀበኛው፣ ሌባው፣ ዘራፊው፣ ቦዘኔው፣ አረመኔው፣ ሽፍጠኛው፣ ቀማኛው፣ ኮንትራው፣ ባንዳው፣ አራዳው፣ ሙንጣዙ፣ ተታላዩ፣የዋሁ፣ አሳዛኙ፣ ግራ የተጋባው፣ ጫት ቃሚው፣ ቡልቅልቅ አድራጊው፤

ዘልዛዩም፣ ቀርጣፊውም፣ ሽርዳጁም፣ ገርዳፊውም፣ ወቃጩም፣ አቡኪውም፣ አንኳሪውም፣ መሬት ሻጩም፣ አሻሻጭ- ደላላውም፣ አገር ታሪክ አዋራጁም፣ የታሪክ አተላውም፣ ትውልድ አራካሹም፣ አጥፊውም፣ መሸተኛውም፣ ለነፍሱ ያደረውም፣ አባ ሰላማውም፣ ለሥጋው የቆመውም፣ ሊቁም፣ ደቂቁም፣ እኔም፣ አንተም፣ እሱም፣ እሷም፣ እናንተም፣ እኛም፣ እነሱም፣ እነዚያም፣ እነዚህም፣ ላይ ያሉትም፣ ታች ያሉትም፣ ገዢም፣ ልግዛ ባይም፣ ተገዥ- ተረጋጭም፣ እረ ስንቱ ሁሉም ፖለቲካኛ ሆኖ ይፏልላል።

የጉድ እኮ ነው! ሬዲዮ፣ ጋዜጣው፣ ኢንተርኔት- ዌብ ሳይቱ፣ ፓል ቶኩ፣ ቻት ሩሙ፣ መድረኩ፣ ቴሌ ኮንፈረንሱ፣ ቴክስቱ፣ ስብሰባው፣ ቤተ ክርስቲያኑ፣ ምግብ ቤቱ፣ ሰርግ ቤቱ፣ ለቅሶ ቤቱ፣ ዝክር ቤቱ፣ ስታር ባኩ፣ ደንከን ዶናቱ፣ ታክሲ ቦታው፣ ፓርኪንጉ፣ ግሮሰሪው፣ ኳስ ሜዳው፣ ኮሚኒቲው፣ በየ ቤቱ፣ ጆሮው፣ የሰራ አካላቱ፣ ኸረ ስንቱ ስልችት ብሎታል።

የጉድ እኮ ነው! ምን ማይሳማ ነገር ቀረ? ወይ ፖለቲካ በቁሟ እንደ ጣቃ ጨርቅ በየአቅጣጫው ትቀደዳለች- ትበሸከታለች።

የጉድ እኮ ነው! መቀደዱንስ ትቀደድ ማን መልክ ሰጥቶ ባለቤቷ ይሆን? ማን ተጠቅሞባት ለግብ- ለፍሬ ያበቃታል?

እንደው የጉድ እኮ ነው! ፖለቲካ ባለቤት፣ አገር ደግሞ ወንድ አጣች።
የጥንቶቹስ ትውልዶች አልቻልኩም መረረኝ እያሉ ዘፈኑ፣ ፎከሩ፤ ኬንያውያንም "ዋፒ ኡሁሩ" እያሉ ለአገር ተጋደሉ እኛስ? እኛስ? እኛስ?

***ክፍል 2 ይቀጥላል..***

**ከአስተዋይ በቀለ**